# Learning by Ear 2013

## "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" – "መዘዙን መቀበል"

## EPISODE 22: የዘሩትን ያጭዳሉ

**AUTHOR: James Muhando**
**EDITORS: Friederike Müller, Maja Braun, Madelaine Meier**
**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**<u>INTRO/OUTRO:</u> NARRATOR**

**<u>SCENE 1: ሉሊት FIGHTS FOR HER BABY</u>**

- **ሉሊት (F, 40)**
- **ፖሊስ ሙሉጌታ (M, 45)**
- **መርማሪ ርብቃ (F, 40s)**

**<u>SCENE 2: ብሩክ AND ቅዱስ DISCUSS CHILD LABOUR</u>**

- **ቅዱስ (M, 8)**
- **ብሩክ (M, 8)**
- **ምህረት (F, 15)**

**<u>SCENE 3: መርማሪ ርብቃ TALKS TO ሉሊት</u>**

- **መርማሪ ርብቃ (F, 40s)**
- **ሉሊት (F, 40)**

**<u>SCENE 4: ዳንኤል SNEAKS TO አልማዝ ROOM AT NIGHT</u>**

- **ዳንኤል (M, 16)**
- **አልማዝ (F, 16)**

## INTRO

## 1. NARRATOR:

**ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ስለ አፍሪቃውያን ታዳጊ ወጣቶች የሚተርከዉና ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉ ተከታታይ ትምህርታዊ ድራማ ነዉ። "መዘዙን መቀበል" በተሰኘዉ ሁለተኛው ዙር ድራማ ክፍል ሃያ ላይ ደርሰናል። ፡፡ ዳንኤል ለጊዜው ከታገደ በኋላ ወደ ቦንጎ አካዳሚ ተመልሷል፡፡ እናም እዛ የሚጠብቁት ሁለት ሴቶች አግኝተውታል፡፡**

### *KW BEGIN*

## 2. EPISODE 20, LINES 115 – 118:

*<u>ምህረት:</u> ሃይ ዳንኤል.*

*<u>ዳንኤል:</u> ኧምም…ሃይ…ሜ…ምህረት? (…)*

*<u>አልማዝ</u>: እንዴት ነህ፣ ዳንኤል!*

*<u>ዳንኤል</u>: አልማዝ? እዚህ ምን ታደርጊያለሽ*

### *KW END*

## 3. NARRATOR:

**ምህረት የዳንኤልን ልጅ ተሸክማለች፡፡ ሌላኛዋ ልጅ አልማዝ ደግሞ ላቦሪያ ውስጥ ፍቅረኛው ነበረች፡፡ አሁን ደግሞ አልማዝ በቦንጎ አካዳሚ የልውውጥ መረሃ-ግብር ተማሪ ናት፡፡ የዳንኤል ችግር ሴቶቹ ብቻ አይደሉም፡፡ አባቱ፣ አቶ ካሳሁን በማዕድን ማውጫ ስፍራው ህጻናትን አስገድደው በማሰራታቸው በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ ከእነዚህ ልጆች መካከልም ከማዕድን ማውጫው አምልጠው ቤታቸው የገቡት የምህረት መንታ ወንድሞች ቅዱስ እና ብሩክ ይገኙበታል፡፡ አባታቸው አቶ ሙላቱ ፖሊስ ጣቢያ**

ታስረዋል። አቶ ሙላቱ የታሰሩት ዘርፊሀል በሚል ሲሆን እርሳቸው ግን የተባለውን ዘረፋ አልፈፀሙም። እንደውም ከእዚህ እሻጥር ጀርባ የአካባቢዉ ባለፀጋ ፖለቲከኛ የአቶ መኩሪያ እጅ ነበረበት።

## 4. EPISODE 12, LINES 48 – 49:

<u>አቶ መኩሪያ:</u> (…) እዚህ ያስገባሁህ ከሚስቴ እና ከልጃችን ጋር አለማችንን መቅጨት እንድንችል እንዳታደናቅፈን ነው። (…)

<u>አቶ ሙላቱ:</u> ሙከራብ፣ ይህንን ማድረግ አትችልም…

## 5. NARRATOR:

በእነምህረት ቤተሰብ ውስጥ ብዙ ነገሮችእየተካሄዱ ነው! እናቷ ወ/ሮ ሉሊት ከዓመት በፊት አዲስ የተወለደችን ሴት ልጃቸውንን አባትዋ አቶ ሙላቱ ፤ ለአቶ መኩሪያ እንደሸጧት አውቀዋል። ወ/ሮ ሉሊት አሁን ልህፃኗን ለማስመለስ እየታገሉ ነው። « የዘሩትን ያጭዳሉ» የተሰኘው ቀጣይ ድራማ ክፍል የሚጀምረዉ ወ/ሮ ሉሊት ፖሊስ ጣቢያ ዉስጥ ሆነው ነዉ።

## <u>SCENE 1: ሉሊት FIGHTS FOR HER BABY</u>

## 6. SFX: POLICE STATION ATMO

## 7. SFX: STEPS - ሉሊት APPROACHING

**8. ሉሊት:** መርማሪ ሙሉጌታ እዚህ የመጣሁት ለልጄ ጉዳይ ነው። ትንሿን ልጄን ማየት እፈልጋለሁ።

**9. ፖሊስ ሙሉጌታ:** **(to himself)** ኤድያ ይህች ሴትዮ እንግዲህ ጀመራት፣ እንደገና መጣች።.

***KW BEGIN*** **(to ሉሊት)** ሉሊት መንግሥቱ ህጻኗ ልጅ የማህበራዊ አገልግሎት ድጋፍ እየተሰጣት መሆኗን ነግሬሻለሁ።.

**10. ሉሊት:** ማህበራዊ አገልግሎት ምንድን ነው? ሁልጊዜ ይህንኑ ትነግረኛለህ፣ የትነው ያለው?

**11. ሙሉጌታ:** **(calmly)** ማህበራዊ አገልግሎት ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ወይም ወላጆቻቸው ያልታወቁ ልጆችን የሚንከባከብ ነው።.

**12. ሉሊት:** ልጄ ወላጅ አላት። እኔ! እዚህ የምመላለሰው ወላጇ ስለሆንኩ ነው። የት እንደሆነ ንገረኝ እና ሄጄ ልጄን አያታለሁ!

**13. ሙሉጌታ:** ቀደም ሲል ነግሬሻለሁ፣ ይህን ማድረግ አልችልም።.

**14. ሉሊት:** ለምን አትችልም? ልጄ ናት፣ እንድትመለስልኝ እፈልጋለሁ።

***KW END***

**15. ሙሉጌታ:** ይህ ጉዳይ እየታየ መሆኑን ነግሬሻለሁ…

**16. ሉሊት:** **(shouts)** ስለ መታየት አትንገረኝ፣ መርማሪ ፖሊስ! ይህን ቃል መስማት ሰልችቶኝ ደክሞኛል። ለብዙ ወራት ይህንኑ ስትነግረኝ ቆይተሀል። ልጄን ማየት እፈልጋለሁ!

**17. ሙሉጌታ:** እመቤት ድምጽሽን ቀንስ። አዲሱ አለቃዬ ትሰማሻለች። እርግጠኛ ነኝ ድምጽሽ አያስደስታትም።

**18. ሉሊት:** **(shouts even more)** ድምጼን እንድቀንስ አትንገረኝ! እንደውም አንተ ልትረዳኝ ባለመቻልህ አለቃህን ማነጋገር እፈልጋለሁ።

**19. ሙሉጌታ:** **(menacingly)** እያስጠነቀቅሁሽ ነው።  መጮኽሽን ከቀጠልሽ አስረን እንዘጋብሻለን።

**20.** ሉሊት: **(screams)** እሰረኝ! ቀጥላ! በገዛ ማህጸኔ ለ9 ወራት የተሸከምኳትን ልጄን ማየት በመፈለጌ,,, ተነስ እስር ቤት ወርውረኝ! ቀጥል አልኩህ እኮ! እሰረኝ!!

**21.** ሙሉጌታ: **(shouts)** ሂይ! ሂይ! ተረጋጊ!

**22. SFX: FOOTSTEPS -** መርማሪ ርብቃ **ARRIVES**

**23.** መርማሪ ርብቃ **:** ኢንስፔክተር ይህ ሁሉ ግርግር ምንድን ነው?

**24.** ሙሉጌታ: **(tries to make light of it)** አትጨነቂ፣ መርማሪ ርብቃ ሁሉም ነገር በቁጥጥር ስር ነው።

**25.** መርማሪ ርብቃ **:** አይመስለኝም። **(to** ሉሊት**)** እመቤት ምንድን ነው ችግሩ?.

**26.** ሉሊት**:** እትዬ እኔ ፣ ለወራት እየተመላለስኩ ል…

**27.** ሙሉጌታ: **(fake laughter )** ሴትዮዋ እብድ ትመስለኛለች፣ እኔ…

**28.** መርማሪ ርብቃ **:** **(firm)** ኢንስፔክተር አንተን አላናገርኩህም። **(politely to** ሉሊት**)** እመቤት ነይ እስኪ ወደ ቢሮዬ ተከተይኝ።..

**29.** ሙሉጌታ: **(to** ሉሊት**)** አለቃዬን ሰምተሻታል ነይ ወደ እርሷ ቢሮ እንሂድ።

**30.** መርማሪ ርብቃ : **(to** ፖሊስ**)** ኢንስፔክተር አንተ እዛው ቆይ፣ ይህችን ሴት ለብቻዬ እናግራታለሁ።

**31.** ሙሉጌታ: ግን እኮ እመቤቴ እኔ ጉዳዩን ተረድቼዋለሁ…

**32.** መርማሪ ርብቃ **:** ኢንፔክተር ትዕዛዝ ነው!

**33.** ሙሉጌታ: እሺ እመቤቴ

**34.** መርማሪ ርብቃ **:** **(to** ሉሊት**)** እሽ ተከተይኝ።.

**35. SFX: FOOTSTEPS ሉሊት AND INSPECTOR መርማሪ ርብቃ**

**36. SFX: DOOR OPENS AND CLOSES**

**37. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 2: ብሩክ AND ቅዱስ DISCUSS CHILD LABOUR</u>**

**38. SFX: TANDIKA SLUMS, INSIDE ምህረት'S HUT**

***KW BEGIN***

**39. SFX: EMPTY METAL BOWLS PUT DOWN ON THE TABLE**

**40. ቅዱስ:** **(sighs in satisfaction)** በጣም ጠገብኩ! አንተስ ብሩክ?

**41. ብሩክ:** **(laughs)** እኔም ቅዱስ። ሆዴ ልክ እንደእህታችን እንደምህረት ሆድ ትልቅ ሆኗል።

**42. THEY LAUGH**

**43. ብሩክ:** እናታችን ከፖሊስ ጣቢያ ከመምጣቷ በፊት የበላንበትን እቃ ብናጥብ ጥሩ ነው። ሳናጥበው  እንዲህከተውነው  ቤት ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ እንደበላን ታይና ትቆጣለች።

**44. SFX: BOWLS CARRIED, SOUND OF UTENSILS BEING WASHED (NOT IN RUNNING WATER)**

**45. ቅዱስ:** ለምንድን ነው ግን በተደጋጋሚፖሊስ ጣቢያ የምትሄደው?

**46.** ብሩክ: አላውቅም፡፡ ምን አልባት አባታችንን ልትጠይቅ ይሆናል፡፡

***KW END***

**47.** ቅዱስ: ብሩክ፣ ወንድሜ፣ ከሆስፒታል በመመለስህ ደስ ብሎኛል

**48.** ብሩክ: እኔም ደስብ ብሎኛል!

**49. SFX: THEY WASH THE UTENSILS**

**50.** ቅዱስ: ብሩክ? አቶ ካሳሁን እና አክስታችን ለምለም አሁን በመያዛቸው ምን ይደርስባቸዋል?

**51.** ብሩክ: አላውቅም፡፡.

**52. SFX: DOOR OPENS AND CLOSES**

**53. SFX: FOOTSTEPS AS ምህረት ENTERS**

**54.** ብሩክ: ምህረት መጣች፡፡ እሷን እንጠይቃት… **(calls)** ምህረት?

**55.** ምህረት: **(from a distance)** ወዬ ብሩኬ!

**56.** ብሩክ: አንድ ሰው በቁጥጥር ስር ሲውል ምን ይሆናል?

**57. SFX: STEPS - ምህረት APPROACHES**

**58.** ምህረት: **(close now)** ያ ማለት በፖሊስ ይያዝና ፍርድ ቤት ይወሰዳል፡፡ ከእዛም ዳኛው ጥፋተኛ መሆኑን ከወሰነበት ይቀጣል፡፡

**59.** ብሩክ: እንደዚያ ከሆነ ጥሩ ነው!

**60. ምህረት:** ለምን ማወቅ ፈለግህ?

**61. ቅዱስ:** ምክንያቱም አክስቴ ለምለም እና ያ አቶ ካሳሁን የሚባለው ሰውዬ ላቦራያ ውስጥ ተይዘዋል።.

**62. ምህረት:** ልክ ነው። እናንተን እና ሌሎች ህጻናትን በማዕድን ስፍራ በማሰራታቸው ነው የተያዙት። የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ይባላል።

**63. ብሩክ:** ያ ማለት እናታችንንም ያስረታል?

**64. ምህረት:** **(irritated)** አይ፤ ለምን?

**65. ብሩክ:** ምክንያቱም ሱቅ ትልከን እና ከበላን በኋላ እቃዎቻችንን እንድናጥብ ታደርገናለች።.

**66. ቅዱስ:** እማዬ እንድትታሰር አልፈልግም።.

**67. ብሩክ:** እኔም ብሆን አልፈልግም።

**68. ምህረት:** **(Laughs)** አታስቡ። እናታችን አትታሰርም። እቤት ውስጥ መርዳት የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ አይደለም!

***KW BEGIN*** ብሩክ መድሀኒትህን ወስደሀል?

**69. ብሩክ:** አዎ፣ ወስጃለሁ። ዶክተር ሮቤል ካልወሰድኩ ሳል እንደሚመለስብኝ ነግሮኛል።

**70. ምህረት:** ልክ ነው፡፡ የሳንባ ነቀርሳ መድሀኒት ዶክተሩ ባዘዘህ መሰረትሳታዛባ መውሰድ አለብህ፡፡ የተሻለህ ቢመስልህ እንኳ ሙሉ በሙሉ ስላላገገምክ መድሀኒቱን ሙሉ ለሙሉ መጨረስ አለብህ፡፡ ሰውነትህ አሁንም ከበሽታው ጋር እየተዋጋ ነው፡፡.

**71. ብሩክ:** አዎ፡፡ አውቃለሁ…

***KW END***

**72. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 3: መርማሪ ርብቃ TALKS TO ሉሊት**

**73. SFX: POLICE STATION ATMO HEARD THROUGH DOOR**

**74. መርማሪ ርብቃ :** ባክሽን ተቀመጭ.

**75. SFX: ሉሊት SITS DOWN ON CHAIR**

**76. መርማሪ ርብቃ :** መርማሪ ርብቃ እባላለሁ እዚህ የተመደብኩት በቅርቡ ነው፡፡ ስምሽ ማን ነበር?

**77. ሉሊት:** ሉሊት እባላለሁ፤ የአቶ ሙላቱ ሚስት ነኝ፡፡.

**78. መርማሪ ርብቃ :** ሙላቱ …ወ/ሮ ሉሊት ባቤትሽ እዚህ እኛ ጣቢያ ውስጥ የታሰረው አይደለም እንዴ? በዘረፋ ወንጀል ተጠርጥሮ ነው አይደል?

**79. ሉሊት:** ልክ ነው፡፡ እዚህ ግን የመጣሁት በእርሱ ምክንያት አይደለም፡፡.

**80. መርማሪ ርብቃ :** አልገባኝም፤ እና ለምን መጣሽ?

**81.** ሉሊት: **(sighs)** የዛሬ አመት ገደማ ሴት ልጅ ወልጄ ነበር፡፡ ባለቤቴ ልጄን ወስዶ ለአካባቢው ፓለቲከኛ ሸጣት፡፡ የት እንዳለች እንዳወቅሁ ወዲያውኑ እዚህ ባመለክትም…

***KW BEGIN***

**82.** መርማሪ ርብቃ : **(surprised)** ይቅርታ-ምን? የተናገርሽው የገባኝ ስላልመሰለኝ እንደገና ትነግሪኛለሽ? ባለቤትሽ ልጅሽን ሸጣት?

**83.** ሉሊት: አዎ፡፡ ባለቤቴ ልጅቷን የማየት እድል ሳይሰጠኝ የሚጠጣበት ገንዘብ ለማግኘት ሲል ሸጣት፡፡

***KW END***

**84.** መርማሪ ርብቃ : ቆይ…ሰውዬው የራሱን ልጅ ሸጠ እያልሽኝ ነው? ያ ህገ ወጥ ጉዲፈቻ ነው! ወንጀል ነው!

**85.** ሉሊት: እኔም የፈፀመው ልክ ነው ብዬ አላሰብኩም፡፡ ግን ልጄ የት እንዳለች ያወቅኩት ከታሰረ በኋላ ነው፡፡

**86.** መርማሪ ርብቃ : የት ነበረች?

**87.** ሉሊት: በአካባቢው የምክር ቤት አባል ፣ አቶ መኩሪያ ቤት፡፡.

**88.** መርማሪ ርብቃ : **(sigh)** ህምምም…አቶ መኩሪያ…

***KW BEGIN***

**89.** ሉሊት: አዎ፡፡ መጥቼ ካሳወቅኩኝ ጊዜ አንስቶ ይኸው መርማሪ መኮንኑ ጉዳዩ እየታየ ነው ይለኛል፡፡.

**90.** መርማሪ ርብቃ : የፖሊስ ስነ-ስርዓት ጊዜ ይፈጃል

**91. ሉሊት:** ግን ብዙ ወራት ሆነ እኮ፡፡

**92. መርማሪ ርብቃ :** እንደዚያ ነው? ቆይ እስኪ መዝገቡን ልየው…

**93. SFX: PAPERS/FILES BEING SHUFFLED**

***KW END***

**94. መርማሪ ርብቃ :** **(to herself)** ጉዳዩ የተመዘገበ አይመስልም…ያልተለመደ ነገር **(to** ሉሊት**)** ነው…እዚህ ምን እየተካሄደ እንደሆነ አላወቅም፣ወ/ሮ ሉሊት፤ ግን አንድ ነገር ቃል እገባልሻለሁ ችግሩን ለማወቅ እና ለመፍታት እሞክራለሁ ፣ ግን ትንሽ ጊዜ እንድትታገሺኝ እጠይቅሻለሁ፡፡

**95. ሉሊት:** **(sighs)**

**96. MUSICAL INTERLUDE**

## <u>SCENE 4: ዳንኤል SNEAKS TO አልማዝ</u>

**97. ATMO: NIGHT; BONGO ACADEMY, OUTSIDE GIRLS’ DORMITORY. SERENE, CRICKETS**

**98. SFX: FOOTSTEPS ON TWIGS AS ዳንኤል SNEAKS TO አልማዝ ROOM**

**99. ዳንኤል:** **(W´whispers to himself)** ኤጭምን አይነት ሲያስጠላ! ማንንም ሳይነጋገሩ እዚህ በብቸኝነት መቆየት የመጨረሻ ይጨንቃል፡፡ በለጠ እንኳ ሊያናግረኝ አልፈለገም፡፡ የልብ ጓደኛዬ እንኳንየነበረ ቢሆንም! ምንድን አይነት ጣጣ ነው…ግን አልማዝ ታናግረናለች ፡፡ አሁንም እንደምትወደኝ እወራረዳለሁ! በእርግጥ ለማስመሰል እየሞከረች ነው፡፡ ዳንኤል ካሳሁንን ግን አትቋቋመውም፡፡ **(laughs)** ክፍሏ ውስጥ እንዳለች ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ….

***KW BEGIN***

**100. SFX: STEPS ON TWIG WHICH SNAPS LOUDLY**

**101.** ዳንኤል: **(urgent)** ወይኔ ጉድ ፈላ! መደበቅ አለብኝ። ጠባቂው ሰምቶኛል መሰለኝ፡ ፡ በሴቶች ማደሪያ አካባቢ ሳልፍ መታየት የለብኝም።

**102. SFX: FAST FOOTSTEPS ON TWIGS AS HE RUNS TO HIDE**

**103.** ዳንኤል: **(pants)** አያይ በጣም አሪፍ… ሲጋራውን እያቦነነ በራሱ ተመስጧል።.

***KW END***

**104. SFX: WINDOW OPENS**

**105.** አልማዝ: **. calls)** እዛ ጋር? ማን ነው?

**SILENCE**

**106.** አልማዝ: በል ማንም ሆንክ  ማንም ወደእዚህ ወጣ በል፣ ወይም እጮሀ እና ጥበቃዉን እጠራለሁ።

**107.** ዳንኤል: **(whispers loudly)** እሽ፣ አልማዝ! አትጩሂ- እኔ ነኝ ዳንኤል።

**108.** አልማዝ: ዳንኤል? በዚህ ምሽት ክፍሌ መስኮቴ አጠገብ ተደብቀህ ምን ትሰራለህ?

**109.** ዳንኤል: **(still whispering)** እሽ፣ ድምጽሽን ቀንሺ።አባክሽን መግባት እችላለሁ?

**110.** አልማዝ: ሙትቻ! አይቻልም! ምን ፈልገህ ነዉ ዳንኤል?

***KW BEGIN***

**111.** ዳንኤል: ላነጋግርሽ እፈልጋለሁ።.

**112.** አልማዝ: ነገ ክፍል ውስጥ ልታናግረኝ ትችላለህ። ደህና እደር ዳንኤል

**113.** ዳንኤል: ያንን ማድረግ እንደማልችል ታውቂያለሽ። የማስጠንቀቂያ ጊዜዬ እስኪያልቅ ድረስ ከአንዲትም ሴት ልጅ ጋር መነጋገር አልችልም። እባክሽን አምስት ደቂቃ ብቻ ስጪኝ።

**114.** አልማዝ: ሶስት ደቂቃ ሰጥቼሀለሁ።

**115.** ዳንኤል: **(relieved)** አመሰግናለሁ አልሚ። መቼም እዚህ ጋር ተገትሬ እንድያዝ እንደማትተይኝ አውቃለሁ… አሁን አስገቢኝ!

**116.** አልማዝ: አይሆንም። ወደ ክፍሌ እንድትገባእማ አልፈቅድልህም! የሚያስፈልግህን እዛው ተናገረህ መሄድ ትችላለህ! በመስኮት ብቅ ብዬ ሳወራህ እንኳን እራሴን አደጋ ላይ ጥዬ ነው።.

***KW END***

**117.** ዳንኤል: **(sighs)** እሺ። አልማዝ፣ ወደ እኔ እንድትመለሺ እፈልጋለሁ።.አልማዝ: ምን? እራስህን አልሳትክም አይደል ዳንኤል?

**118.** ዳንኤል: አልማዝ ከምህረት ጋር ስለተፈጠረው ነገር አዝናለሁ። ተጸጽቻለሁ! ለእኔ ምኔም አይደለችም!

**119.** አልማዝ: ዳንኤል፣ ስታስጠላ! ማድረግ የምትችለው ትንሹ ነገር በጥፋትህ መቀጠልህ ነው! ቆይ ቆይ ግን ይህንን ሁሉ ካደረግህ በኋላ በቀጥታ እንድመለስልህ ማሰብህ ምን ያህል ደፋር ብትሆን ባክህ?

**120.** ዳንኤል: ማ…ማለቴ፣ እኔ እና አንቺ የመጣነው ከአንድ ሀገር ነው። አንድ ላይ መሆን አለብን።

**121.** አልማዝ: ዳንኤል አፍቅሬህ ነበር። እዚህ መጥቼ ከአንተ ጋር ለመሆን የዝውውር መርሀ ግብሩን ለማግኘት ብዙ ዉጣ ዉረድ አሳልፌያለሁ። ሌሎች ሴቶችን በማሳደድ ስራ እንደበዛብህ አውቄ ቢሆን ኖሮ ጦርነቱ ከዚህ ቢብስ እንኳ ላቦሪያ ውስጥ እቀር ነበር። በቃ አንቅሬ ተፍቼያለሁ። ደግሜ ላነጋግርህ አልፈልግም!

**122.** ዳንኤል: አልሚ በእናትሽን…

**123.** አልማዝ: ሂድልኝ በቃ፣ ዳንኤል።.

**124. SFX: WINDOW SLAMS**

**125.** ዳንኤል: **(shouts)** እሺ ቆይ አልማዝ…ትንሽ ገንዘብ እፈልጋለሁ!

**126. SFX: WINDOW OPENED AGAIN**

**127.** አልማዝ: ኦሀ፣ ገባኝ። ያ ሁሉ ዳርዳታ ለዚህ ነበር! አሁን ነገር ሳታበዛ ሂድ፣ ዳንኤል። ጥበቃው እንደሚይዝህ ተስፋ አደርጋለሁ!

## 128. OUTRO - NARRATOR:

**ዳንኤል በቀድሞ ጓደኛው በአልማዝ ተባርዋል። ግን አንድ ጊዜ- ከጥቂት ወራት በፊት ልክ እንደዚሁ ለምህረት ተመሳሳይ ነገር ብሏት ነበር፣ አይደለም እንዴ? አልማዝ የቀድሞ ፍቅረኛዋ እንዲያ በምሽት መኝታ ቤቷ ህንፃ ስር በመምጣቱ ምን እንደተሰማት እንዲሁም በተጨማሪ ምን እንደሚያስጨንቃት ለማወቅ የዕለት እንቅስቃሴዋን ለግሏ በምትቀርጽበት የቪዲዮ ዘገባዋ  ላይ ይመልከቱ። የዛሪዉን የቪዲዮ ዘገባውን በድረ-ገጽ አድራሻችን dw.de/lbe ላይ ያገኙታል። እንደተለመደው አስተያየታችሁንበፊስ ቡክ ገጻችን ላይ ልታሰፍሩ ትችላላችሁ።  የሚቀጥለውን ክፍልም ሊከታተሉን እንደሚችሉ አይዘንጉ። ጤና ይስጥልን!**